Government of South Australia
Department for Education

**Office of the Chief Executive**

31 Flinders Street
Adelaide SA 5000

GPO Box 1152
Adelaide SA 5001
DX 541

www.education.sa.gov.au

ወድ ወላጆችና አሳዳጊዎች፣

ኮሮና ቫይረስ (COVID-19) እንደ ግለሰብ፤ እንደ ቤተሰብ እና እንደ ማህበረሰብ የተለያዩ ተግዳሮቶችን ጥሎብናል።

አስተማሪዎቻችን እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻችን በሁኔታው ላይ ዝግጁ መሆናቸውን ስንገልጥላችሁ በኩራት ነው።  እንደ ማንኛውም የህብረተሰብ አባል ጭንቀቱ ሊኖራቸው ቢችልም፤ ለተማሪዎቻቸው ቀጣይ ትምህርት መስጠትን ተቀዳሚ ተግባራቸው አድርገውታል።

ትምህርት ቤቶችና ቅድመ ትምህርት ቤቶች በጣም አስፈላጊ አገልግሎቶች ናቸው። በአውስትራሊያ ዙሪያ የሚገኙ ሁነኛ የሕዝብ ጤና በለሙያዎች ምክር፣ ትምህርት ቤቶች ክፍት እና ተከፍተው መቆየት እንደሚችሉ ገልጸዋል።

በተሰጠውን የጤና ምክር፣ መመሪያና ማሳሰቢያ እየተከተልን፣ በክፍል ውስጥና በመጫወቻ ቦታዎች ማህበራዊ (የአካል) ርቀትን እና የንጽህና ልምዶችን እንተገብራለን። ጥራት ያለው ትምህርት መስጠታችንን በመቀጠል፣ የተማሪዎቻችን፣ የሰራተኞቻችን እና የትምህር ቤቱ ማህበረሰብ ደህንነትና ጤንነት ከፍተኛ ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው።

የኮሮና ቫይረስን (COVID-19) መዛመት ለመግታት ብዙዎች በቤት ውስጥ እንዲቆዩ ቢደረግም፣ እኛ ግን ቆመን አንቆይም።

በዚህ ክፍለ አህጉር ለሚገኙ ልጆቻችን እና ወጣት ሰዎች ትምህርቱ እንዲቀጠል ማድረግ ዋናው ትኩረታችን ነው። በዚህ ከዚህ በፊት ገጥሞን በማያውቅ ገጠመኝ፣ መምህራኖቻች፣ የመዋእለ ህፃናት አስተማሪዎቻች፣ ርእሰ መምህራኖች እና የክፍል ሠራተኞች የትምህርት አቅርቦታችንን በመቀያየር፣ ቤተሰቦችን እና አሳዳጊዎችን በመደገፍ እናገለግላለን።

ባለፈው ሳምንት የኛ መማር በደአ (Our Learning SA) የሚል ድረገጽ ጀምረናል። ልጆችን እና ወጣት ሰዎችን በቤታቸው ውስጥ ለትምህርታቸው እንዲረዳቸው በማሰብ፣ ድረገጹ ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ የመማሪያ መገልገያዎችን ጭነናል። ከተጨመሩት መካከል፣ ከፍተኛ ጥራት ካላቸውና ተማሪዎችን በትምህርታቸው ሊረዱ ከሚችሉት የኤቢሲ ቲቪ መርሃግብሮች (ABC TV programs) ጋር ተጣምረዋል። ድረገጹ በተከታታይ ስለሚያድግ እባክዎን በ www.ourlearning.sa.edu.au ላይ ይሞክሩት።

በተጨማሪም በድረገጹ ላይ ‘ለቤተሰቦች ምክር’ የሚል ክፍል ፈጥረናል፤ እሱም ለተማሪዎችና ለቤተሰቦች ቪዲዮዎችና የእውነታ የወረቅት መልእክቶችን ጨምረናል። እነሱም የሚከተሉትን ይጨምራል፡

- የመማሪያ አካባቢዎችን ማዘጋጀት
- በቤት ውስጥ ሆነው በሚማሩበት ጊዜ ደስተኛና ጤናማ እንዲሆኑ ማድረግ
- ቤት ውስጥ ከልጆችዎ ጋር ማንበብ
- በመስመር ላይ (online) እንዲማሩ ማዘጋጀት
- ልጆችዎን ስለ ኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ያነጋግሯቸው

ትምህርት ቤቶችና ቅድመ ትምህርትቤቶች በርቀት የማስተማርን ተግባራዊ ለማድረግ በተለያየ ደራጃ ላይ ናቸው። በተጨማሪም፣ ሁሉም ልጅ በቤቱ ውስጥ ኮምፒዩተርና ኤነተርኔት እንማይኖረው እናውቃለን።

በዚህ ሳምንት፣ በተማሪዎች ነፃ ቀናት፣ መምህራኖቻችን የቤት ውስጥ ትምህርትን ወደሚቀጠለው ደረጃ ይወስዱታል።

ቨርቹዋል (virtual) ክፍሎችን ለእያንዳንዱ አስተማሪዎቻችን እንዲደርስ እናደርጋለን፣ በተጨማሪም ኮምፒውተር ወይም ኢንተርኔት የሌላቸውን ልጆች ከክፍላቸው ጋር የሚገናኙበትን መንገድ እያጣራን ነው። ይህ ደግሞ መምህራኖች ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በማሰብ በሥራ ተጠምደው ባዘጋጁት በወረቀት ላይ ከታተመው የመማሪያ መገልገያ ጋር እጅ ለእጅ በመሆን ያገለግላል።

ያለማቋረጥ ሠራተኞቻችን እና አስተማሪዎቻችን በመተባበር ለ2ተኛው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በሚያደርጉት ዝግጅት ተደንቀናል። በዚህ ጉዳይ ሁላችንም አንድ ላይ ነን።

ተጨማሪ ድጋፍ ካስፈለገዎ ወይም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ከልጅዎ አስተማሪ ጋር አብረው ይሥሩ።

በአክብሮት የእርስዎ፣

Hon John Gardner MP
**Minister for Education**

7 ኤፕሪል 2020

Rick Persse
**Chief Executive**

7 ኤፕሪል 2020